# ሀገር አቀፍ የሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኤክስፖ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ ስለማድረግ

**በ2016ዓ.ም በግንቦት ወር ለሚካሄደዉ ሀገራዊ የሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኤክስፖ ላይ መወዳደር የሚትፈልጉ ችግር ፈቺ የምርምርና የፈጠራ ሥራ ያላችሁ ተቋማት፣ ተመራማሪዎችና የፈጠራ ባለሙያዎች ከታች በተዘረዘረዉ መስፈርት መሰረት እንዲትሳተፉ ጥሪ እናደርጋለን።**

## የፈጠራ ስራ ያላቸው ግለሰቦች እና ተቋማት ሊያሟሏቸው የሚገቡ ግዴታዎች

1. ቋሚ መኖሪያው/ዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው/ያላት፤
2. የፈጠራ ስራው በመንግስት የትኩረት አቅጣጫ በሆኑት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ውስጥ የሚካተት፤
3. የፈጠራ ስራ ባለሙያዎችና ተቋማት ግኝታቸውን በተመለከተ የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችሉ፤
4. የፈጠራ ስራው በጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ችግር ፈቺ ስለመሆኑ ከተጠቃሚ ድርጅቶች/ ተቋማት የማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል፤
5. ቴክኖሎጂዎችን በማላመድና በመጠቀም ለውጥ ያመጣ/ች፤
6. የፈጠራ ስራዎቹ በተጨባጭ የህብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ ወይም የፈቱ ሊሆኑ ይገባቸዋል።

## የግል ወይም የቡድን ተወዳዳሪ ተመራማሪዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ግዴታዎች

1. ቋሚ መኖሪያው/ዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው/ያላት፣ ወይም የምርምር ውጤቱ በቡድን ከተሰራ የቡድኑ አባላት መኖሪያቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ እና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው፤
2. የሚወዳደርበት/የምትወዳደርበት የምርምር ውጤት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሆነ፤
3. የምርምር ውጤቱ ለተጠቃሚው የተሠራጨና ጥቅም ላይ የዋለ፤
4. የምርምር ውጤቱ በጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ችግር ፈቺ ስለመሆኑ ከተጠቃሚዎችና ድርጅቶች/ተቋማት የማረጋገጫ ደብዳቤ የሚያቀርብ/የምታቀርብ፤
5. የምርምር ውጤቱ ከዚህ በፊት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሀገር አቀፍ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሽልማት ያልተሸለመ፤
6. የምርምር ውጤቱ የሀገራችንን የወቅቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎት ክፍተት የሚሞላ፤
7. ተወዳዳሪዎች ስለ ምርምሩ አካሄድና ውጤት ማለትም፡-
   - ምርምሩ የሚፈታው ችግር (Statement of the Problem)፤
   - ምርምሩን ለማከናወን የተጠቀሙበት ዘዴ፤
   - የምርምሩ ወሰን፤
   - በምርምሩ የተገኘው ዕውቀት/ቴክኖሎጂ፤
   - የተገኘው ዕውቀት/ቴክኖሎጂ ከዚህ በፊት ከነበረው ቴክኖሎጂ ጋር ሲነጻጸር ያለው ጠቀሜታን በማካተት አጭር የፅሁፍ መግለጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ተወዳዳሪ ተመራማሪዎች፣ የፈጠራ ባለሙያዎች እና ተቋማት የሽልማት መመሪያዎች፣ የማመልከቻ ቅፃቅፆች **ከአ/ምንጭ ዩኒቨርሲቲ-እንዱስትሪ ትስስርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዋና ዳይሬክተር** ጽ/ቤት በአካል በመምጣት ወይም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዌብ ሳይት http://www.mint.gov.et ማግኘት የምትችሉ ሲሆን ማመልከቻችሁን እስከ ግንቦት 10/2016ዓ.ም ለአ/ምንጭ ዩኒቭ-እንዱ/ትስ/ቴክ/ሽግ/ ዋና ዳይ/ጽ/ቤቱ (የአስተዳደር ሕንፃ ቢሮ ቁጥር 111) ማስገባት የሚትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

ለዝርዝር መረጃ በስልክ ቁጥር **0911795851** ደዉሎ መጠየቅ ይቻላል።